# የ COVID ክትባት ካርድዎን አግኝተዋል፡ አሁን ምን ይቀጥላል?




የ COVID-19 ክትባትዎን ሲወስዱ ይህንን የሚያረጋገጥ የክትባት ካርድ ይሰጥዎታል፡፡ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ያስቀምጡት! የክሬዲት ካርዶችዎ ፣ የመንጃ ፈቃድዎ ወይም ፓስፖርትዎ እንደሚይዙት ሁሉ ሊያዙት ይገባል፡፡ ካርድዎ የጊዜ መርሐግብር አስታዋሽ ብቻ አይደለም፤ ለጉዞ ፣ ዝግጅቶች ላይ ለመሳተፍ እና ምናልባትም በኋላ ጥንካሬ ከፍ ለማድረግ የሚያስፈልጉዎት ይፋዊ መዝገብ ነው።

ብዙ የዋሽንግተን ንግዶች እንደ ቅናሾች ፣ ነፃ ክፍያዎች ወይም ለዝግጅቶች ተመራጭ መቀመጫ ያሉ ማበረታቻዎችን ሙሉ የክትባት ማረጋገጫ ለሚያቀርቡ እየሰጡ ነው፡፡ እነዚህን ልዩ ቅናሾች በአግባቡ **ለመጠቀም የክትባት** ካርድዎን በደንብ ይያዙ፡፡ሙሉ የክትባት ማረጋገጫ

## የክትባት ካርድዎን በሚይዙበት ጊዜ ልብ ሊሏቸው የሚገቡ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እዚህ አሉ:



- **የክትባት** ካርድዎን በክትባት ዙሮች መካከል እና ከዚያ በኋላም ያስቀምጡ፡፡
- **የዲጂታል** ቅጅ በቅርቡ እንዲገኝ የካርድዎን የፊት እና የኋላ ፎቶ ያንሱ፡፡ እንደገና በቀላሉ ለማግኘት እንዲችሉ ቅጂውን ለራስዎ በኢሜል መላክ ፣ አልበም መፍጠር ወይም በፎቶው ላይ መለያ ማከልን ያስቡበት፡፡
- **አንድ** መያዝ ከፈለጉ ፎቶ ኮፒ ያድርጉ፡፡




- **እንዳይጥሉት** ወይም እንዳይጠፋብዎት!!
- **የክትባት** ካርድዎን የሚያሳዩ የራስ ፎቶን ኦንላይን አይለጥፉ። ይልቁንም የራስ ፎቶን ያንሱ እና #vaccinate-WA ወይም #wadoh በመፈለግ **ዲጂታል ተለጣፊ (እስቲከራችንን)** ይጠቀሙ! @WADeptHealth ንን መለያ ማድረግ አይርሱ፡፡
- **ዋናውን** ካርድዎን በፕላስቲክ አያሽጉት፡፡ ሁልጊዜ ሚይዙት ፎቶ ኮፒውን በፕላስቲክ ማሸግ ይችላሉ፡፡




## የ CDC (የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከላት) ክትባት ክርድዎ ከጠፋብዎት ምን ይፈጠራል?

ካርድዎን ሌላ ቦታ ካስቀመጡት ወይም ከጠፋብዎት አይጨነቁ! ይፋዊ፣ የተረጋገጠ የ COVID-19 ክትባትዎን ኦንላይን በነፃ ማግኘት ይችላሉ፡፡ የ MyIR ድህረ-ገጽ በ Washington ግዛት ውስጥ የክትባት ማረጋገጫ ለማግኘት ይፋዊ የግዛቱ መንገድ ነው። ቅጂዎን ለማግኘት www.MyIR-mobile.com ወይም wa.MyIR.net ንን ይጎብኙ እና በነጻ ይግቡ፡፡ አስቀድመው የ MyIR ሂሳብ ካለዎት ሁሉም ተስተካክሏል ማለት ነው!

*እባክዎን በ MyIR በኩል ለመዛግብት ማረጋገጫ ወዲያውኑ ላይሆን እንደሚችል ያስታውሱ እና መዳረሻ በአሁኑ ጊዜ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቻ የተወሰነ ነው።

ለቋንቋ እገዛ ወይም መዝገብዎን ለማግኘት ተጨማሪ እርዳታ ለማግኘት የ Washington ግዛት Office of Immunization and Child Profile (የክትባትና የሕፃናት መረጃ ቢሮ) በመደበኛ የሥራ ሰዓቶች በ 360-236-3595 ይደውሉ ወይም በ waiisrecords@doh.wa.gov ኢሜል ያነጋግሩ፡፡

Washington State Department of Health

DOH 348-809 May 2021 Amharic

ይህንን ሰነድ በሌላ አይነት ለመጠየቅ በስልክ ቁጥር 1-800-525-0127 ይደውሉ፡፡ መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት ችግር ያለባቸው ደንበኞች፣ እባክዎን ለ 711 (ዋሽንግተን ሪሌይ) ይደውሉ ወይም ለ civil.rights@doh.wa.gov ይላኩ።